# ከእግዚአብሔር የተላከ የፍቅር ደብዳቤ

*ልጄ ሆይ፤*

አንተ ባታውቀኝም እኔ ሁለመናህን አውቃለሁ።

መዝ 139፡1

መቀመጥህንና መነሣትህንም ጭምር።

መዝ 139፡2

መንገዶችህም ሁሉ ከእኔ የተሠወሩ አይደሉም።

መዝ 139፡3

ፀጉርህን እንኳ እያንዳንዱን በቁጥር አውቃለሁ።

ማቴ 10፡29-31

በራሴ መልክ አድርጌ ፈጥሬሃለሁና።

ዘፍ 1፡27

የምትኖረውና የምትንቀሳቀሰው ያለኸውም በእኔ ነው፤

ውድ ልጄ ነህና።

ሐሥ 17፡28

ከመፀነስህ በፊት አወቅሁህ።

ኤር 1፡4-5

ፍጥረትን ሳቅድ አንተንም ወሰንሁህ፤ መረጥኩህም።

ኤፌ 1፡11-12

ከመወለድህም በፊት የሕይወት ዘመኖችህን ሁሉ በመዝገቤ አሰፈርቸው።

መዝ 139፡15-16

የትውልድህንም ጊዜና የምትኖርበትን ቦታ አስቀድሜ ወሰንኩ።

ሐሥ 17፡26

ግሩምና ድንቅ አድርጌ ፈጠርሁህ።

መዝ 139፡14

በእናትህም ማህፀን ውስጥ አበጃጅቼ ሠራሁህ።

መዝ 139፥13

በእኔም ፈቃድ ተወለድህ።

መዝ 71፥6

የእኔን ማንነት የማያወቁ ግን ይኸንን አልተረዱም።

ዮሐ 8፥41-44

እኔ የፍቅር እንጂ የቁጣ ነፀብራቅ አይደለሁም።

1 ዮሐ 4፥16

እኔ አባትህ አንተም ልጇ በመሆንህ፤ ፍቅሬን አትረፈረፍኩልህ።

1 ዮሐ 3፥1

ምድራዊ ወላጆችህ ሊሰጡህ ከማይችሉት ስጦታ አብልጬ ሰጠሁህ።

ማቴ 7፥11

ፍጹም የሆንኩ አባትህ በመሆኔ።

ማቴ 5፥48

በጎ ስጦታና ፍጹም በረከት ሁሉ ከእኔ ወረዱልህ።

ያዕ 1፥17

የሚያስፈልጉህን ሁሉ አበረከትሁልህ።

ማቴ 6፥31-33

ለአንተ ያለኝ ዕቅድ በተስፋ የተሞላና ፍጻሜውም ያማረ ነው።

ኤር 29፥11

በዘላለማዊ ፍቅሬ ወደድሁህ።

ኤር 31፥3

ለአንተ ያለኝ በጎ ሀሳብ በቁጥር አይተመንም።

መዝ 139፥17-18

በዝማሬም በአንተ ላይ ከብሬ ደስ ይለኛል።

ሶፎ 3፥17

መልካምን ለአንተ ከማድረግ አልቆጠብም።

ኤር 32፡40

የተወደድህ ርስቴ ነህና።

ዘፀ 19፡5

በፍጹም ልቤና በፍጹም ነፍሴ በምድር ላይ ልተክልህ ፈቃድኛ ነኝ።

ኤር 32፡41

አንተም የማታውቀውንና የማይመረመረውን ነገር ሁሉ እገልጽልሃለሁ።

ኤር 33፡3

በፍጹም ልብህና በፍጹም ነፍስህ ብትፈልገኝ ታገኘኛለህ።

ዘዳ 4፡29

በእኔ ደስ ይበልህ፤ የልብህንም መሻት እሰጥሃለሁ።

መዝ 37፡4

መፈለግንና ማድረግን በበጎ ፈቃዴ በአንተ ውስጥ የማስቀምጥ እኔ ነኝ።

ፊል 2፡13

ከምታስበው ሁሉ በላይ እጅግ አብልጬ ላደርግልህ እችላለሁ።

ኤፌ 3፡20

ከእኔ የበለጠ ሊያበረታታህ የሚችል ሌላ የለምና።

2ተሰ 2፡16-17

በችግርህ ውስጥ የማጽናናህና የማበረታታህ እኔ አባትህ ነኝ።

2ቆሮ1፡3-4

ልባቸውም ለተሰበረ ሁሉ ቅርብ ነኝ።

መዝ 34፡18

ጠቦቶቹን በዕቅፉ እንደሚሰበስብ እረኛ እኔም አንተን እንደዚያው አቀፍኩህ።

ኢሳ 40፡11

እንባዎችህን ከዓይኖችህ አብሳለሁ።

ራእ 21፡3-4

በምድር ላይ የደረሰብህን ስቃይ ሁሉ አስወግዳለሁ።

ራእ 21፡3-4

እኔ አባትህ ነኝና ልጄን ኢየሱስን በወደድኩት ልክ አንተንም ወደድኩህ።

ዮሐ 17፡23

ለአንተ ያለኝ ፍቅር በክርስቶስ ተገልጦአልና።

ዮሐ 17፡26

እርሱ የክብሬ ነፀብራቅና የባሕርዬ ትክክለኛ ምሳሌ ነው።

ዕብ 1፡3

የላክሁትም እኔ ከአንተ ጋር እንደሆንኩ እንጂ ተቃዋሚህ እንዳልሆንኩ እንዲመሰክርልህ ነው።

ሮሜ 8፡31

በደልህንም እንደማልቆጥርብህ እንዲነግርህ ነው።

2ቆሮ 5፡18-19

የሞተውም አንተን ከእኔ ጋር ለማስታረቅ ነው።

2ቆሮ 5፡18-19

የመስቀል ሞቱም እኔ ለአንተ ያለኝን ዘለዓለማዊ ፍቅር ይገልጻል።

1 ዮሐ 4፡10

እነሆ የአንተን ፍቅር ለማግኘት ስል ያለኝን ሁሉ ሳልሳሳ ሰጠሁህ።

ሮሜ 8፡31-32

እንግዲህ ልጄን ክርስቶስን ብትቀበል እኔን ትቀበላለህ።

1 ዮሐ 2፡23

ከእኔም ፍቅር ሊነጥልህ የሚችል ምንም ኃይል አይኖርም።

ሮሜ 8፡38-39

ወደ እኔ ና፤ እኔም በሰማይ ታላቅ የደስታ ግብዣ አደርግልሃለሁ።

ሉቃ 15፡7

እኔ ለአንተ የዘለዓለም አባትህ ነኝ።

ኤፌ 3፡14-15

አንተስ የእኔ ልጅ መሆንህን ትቀበላለህን ?

ዮሐ 1፡12-13

መልስህን በጉጉት እጠባበቃለሁ።

ሉቃ 15፥11-32

*ሁሉን ቻይና አፍቃሪህ የሆንኩት አባትህ*

*እግዚአብሔር ነኝ*